# ታቦትና :ባሊስትራ

አንድ ቀልድ ትዝ አለኝ፡እንዲህ ነበር ትምህርታዊ ቀልዱ፡፡ከብዙ መቶ አመታት በፊት ቫቲካን ወስጥ ይኖሩ የነበሩት ይሁዳዎች ሁሉ ተጠራርገው ከቫቲካን እንዲወጡ ጳጳሱ ይወስናሉ፡፡ድርጊቱን በማውገዘ የአይሁድ ማህበረሰቡ ስብስብ ፣ ወሳኔውን በጽኑ በማውገዝ አመጽ ያቀጣጥላሉ፡፡

በዚህ የተነሳ ሊቀጳጳሱ አመጹን ለማርገብ ሲሉ፣ ድርድር ከይሁዳዎች መሪ ጋር ይዋዋላሉ፡፡ይሁዳዎቹ ቫቲካን እንዲኖሩ ለመወሰን ወይም ለቀው እንዲሄዱ ለማድረግ ሀይማኖታዊ እሰጥ አገባ ወይም ውይይት ማድረግ አለብን ይላሉ ጳጳሱ ፡፡ ይሁዳዎች ካሸነፉችሁ እዚሁ ትቀራላችሁ፣እኛ ደግሞ ካሸነፈን ለቃችሁ ትሄዳላችሁ በማለት፡፡

ለዚህ ሀይማኖታዊ እሰጥ አገባ ይሁዲዎቹ ምንም አማራጭ ስላጡ ከመሀላቸው በድሜ የገዘፉ አንድ ራቢ ሙሼ የሚባሉ ሰው ይመርጣሉ፡፡ ራቢ ሙሼ ላቲን ቋንቋን በወጉ የማይችሉ ቢሆንም በሀይማኖተኝነታቸው ግን የተከበሩ ሰው ነበሩ፡፡ ጳጳሱም በምርጫው ይስማሙና እሰጥ አገባው ግን መሆን ያለበት፣ ድምጽ ሳያሰሙ መስማትና መናገር እንደተሳናቸው ሰዎች ንግግር በእጅ ጥቅሻ ብቻ እንዲሆን ይስማማሉ፡፡

እሰጥ አገባውን ለመጀመር በአንጻራዊ ሥፍራ ጳጳሱና፣ራቢ ሙሼ ከተቀመጡ በኋላ ፣ጳጳሱ እጃቸውን በማንሳት የመጀመሪያውን ሀይማኖታዊ ጥያቄ ሶስት ጣቶቻቸውን በማሳየት ያቀርባሉ፡፡ራቢ ሙሼም የጳጳሱን ሶስት ጣቶች ካዩ በኋላ፣በተራቸው አንድ ጣታቸውን ያሳያሉ፡፡በመቀጠልም ጳጳሱ እነኛኑ ጣቶቻቸውን ባናታቸው ዙርያ በማዞር እንደገና ሁለተኛ ጥያቄያቸውን ያቀርባሉ፡፡ራቢ ሙሼም አሁንም ያወጡትን አንድ ጣታቸውን ወደ መሬት በመጠቆም ያሳያሉ፡፡በመጨረሻም ጳጳሱ ህብስትና፣ የወይን ጠጅ ያመጡናያሳያሉ፣ ራቢ ሙሼም አንድ በለስ ያወጡና በተራቸው ያሳያሉ፡፡በዚህ ወቅት ጳጳሱ ከመቀመጫቸው ይነሱና በውነትም ይህን ራቢን አልቻልኩትም ስለዚህ ይሁዳዎች ቫቲካን መኖር ትችላላችሁ በማለት ይወስናሉ፡፡

ከአንድ ሰአት በኋላ ካርዲናሉ ምን እንደተፈጠረ ጳጳሱን ይጠይቃሉ፡፡ጳጳሱም በመጀመርያ ሶስት ጣቴን አሳየሁት ማለትም አብ፣ወልድ፣መንፈስ ቅዱስን፣ ሥላሴን ለማሳየት ስል፡፡ራቢኑም ለዚያ ምላሽ ሲል፣ አንድ ፈጣሪ ብቻ እንዳለ ለማሳየትና ለሁለቱም ሀይማኖቶች የጋራ መገለጫ የሆነውን አንድ እግዚአብሄርን ለመግለጽ ሲል አንድ ጣቱን አሳየኝ፣ከዚያም በመቀጠል ያወጣሁዋቸውን ጣቶቼን በአናቴ ዙርያ በማዞር እግዚያብሄር በዙሪያችን እንዳለ አሳየሁት፣እሱም በምላሹ፣ጣቱን ወደ መሬት ጠቁሞ እዚህ እፊታችንም እግዚአብሄር አለ ብሎ አሳየኝ፣በመጨረሻም ህብስትና ወይን አውጥቼ ፈጣሪ በደላችንን ለመሻር የተጠቀመበትን ምሳሌ ሳሳየው ፣ እሱም በምትኩ በለስ አውጥቶ አሳየኝ ይህም የመጀመርያውን የሰው ልጆች ሀጥያት መነሻ ለማሳያ የተጠቀመበት ምሳሌ ስለነበር በነገሩ ተደንቄ ተረታሁ በማለት ይመልሳሉ ለካርዲናሉ፡፡

በሌላ በኩልም የአይሁድ ማህበረሰቡም በመሰብሰብ ራቢን ሙሼን እንዴት ቢያደርጉ ነው የረቱት እያሉ ይጠይቋቸው ጀምር፡፡በመጀመርያ ይሁዳዎች ሶስት ቀን ብቻ ነው የቀራችሁ ከዚህ ተጠርጋችሁ ልትወጡ አሉኝ፣እኔም አንዳችንም ነቅነቅ አንልም አልኳቸው፡፡በመቀጠልም ይህ ቅዱስ ስፍራ ከይሁዳዎች መጽዳት አለበት አሉኝ፣ማንም ከዚህ አሁን ካለሁበት ሥፍራ አያስነሳኝም አልኳቸው፣ ከተሰብሳቢው መሀል አንዲት ይሁዳ ሴት ጣልቃ በመግባት ከዚያስ በኋላ? ስትል ራቢኑን ጠየቀቻቸው፣እንጃ !በመጨረሻ ጳጳሱ ራታቸውን አወጡ እኔም በለሴን፡፡

ሀገር ያለደረሰኝ ስናስረክብ ያለዉን እውቁን የጦቢያ ብዕረኛ ፀጋዬ ገ/ እርአያን አስታወስኩት ፡፡ሁሉም በቆመበት ተሸጧል ፡፡በህይወት ያሉት እናቶቻችንና፣አባቶቻችንም ቢሆኑ በቆሙበት ተጠግረዋል፡፡ የሞቱትም ሳይቀር የመካነ መቃብራቸው ስፍራ ተሸቅጧል፡፡ በወያኔ ዘመነ አገዛዝ ፣ ያልተሸጠ፣ያልተለወጠ ነገር የለም፣ የወያኔ ቋት እስኪሞላ ድረስ!!

ካርታ አለኝ ይዞታው የኔ ነው÷ማለት አብቅቶለታል፡፡ለኦርጅናሌው ካርታ፣አስመሳዩ ካርታ ተዘጋጅቶለታል፣ለብሄራዊ ባንኩ መጠባበቂያ የእሴት ወርቃችን ባሌስትራ ተጋድሞለታል፣ለታሪካዊው የሙሴ ጽላታችን ምስለኔ ታቦት ተቀምጦለታል፡፡ባጠቃላይ ለሀገሪቱ ንብረት የወፍጮ ቤት ካርኒ የምታህል ትንሽ ብጫቂ ወረቀት ደረሰኝ እንኳ የለችንም፣ ሀገርንም ሀብታችንንም ያለደረሰኝ ለጉልበተኛ አስረክበናል፡፡

እንደሰሞኑ የውጭ ጋዜጣ ዘገባ መሰረት ከሆነ አባ ጳውሎስ ምላሳቸው ካንድ ምላስ ወደ ታንጎ ምላስነት ተቀይሯል ፡፡ለንስሀ ልጃቸው ለኢትዮጵያ ትቅደም ድረ ገጽ ባለቤት ለአቶ ቢንያም የሰጡት የቃለ መጠይቅ መልስና፣ ለጀርመን ድምጽ ሬድዮ የሰጡት መልስ እውነታውን ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

አባ ዘወትር ቋንቋ እያንሸዋረረች በምታስቸግረው ጥልያን፣ዳግም የውጫሌ ውል ትርጉም ተዛብቶብኝ እንጂ እኔ ከአፌም አልወጣ እያሉን እያስተባበሉ ነው ፡፡ የአባ ካቢኔ ደግሞ ሰሞኑን የቀደመውንም ወንጀላቸውን፣ የአሁኑንም የጥልያን ጉዞ አስመልክቶ ሥልጣነ መንበራቸውን የሚያንገጫግጭባቸው ዶሴ በመምዘዙ፣ ልክ እንደ አቶ መለስ እሳቸውም በተቀናቃኞቻቸው ላይ ካምስት ኪሎ እጨጌ ሳሎናቸው ሆነው የሰልፍና፣የሰአት እላፊ አትውጡ አዋጅ አውጀውባቸዋል፡፡

የተቀናቃኙ ቡድን መሪ ፣ አቡነ ሳሙኤል ትግራዋይ ቢሆኑም፣ ሥረወ ዘራቸው ከአድዋ ካልሆነ ግን ሥራቸው ያወጣቸዋል፡፡ እንደ Grant Jeffrey አባባል ከሆነ በ1991 ዓ.ም የእሥራኤል ኮማንዶዎች ጽላተ ሙሴን ወደ እስራኤል እንደወሰዱት ነው የሚያወሱት፡፡ይህ የአገዛዝ ዘመን ደግሞ የነማን ዘመን እንደሆነ በግልጽ የታወቀ ነው፡፡ጠቅላይ ሚንስትሩ ከአድዋ፣ሊቀ ጳጳሱም ከአድዋ፡፡ባጠቃላይ አድዋ ድርድር፡፡

የሚገርመው የሙሴን ጽላት ሲጠብቁ የነበሩት አባት ጾምያደቀቃቸው፣ በአካል ሥስ፣ የደከሙ አባት እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ የእሥራኤል ኮማንዶ ለእኚህ ርጅና ለተጫጫናቸው አረጋዊ ሰው ለምን እንደአስፈለገ አልገባንም? ለኚህ አባት እኮ ሩስያ የቼቼንያን አማጽያን ለማንበርከክ የተጠቀመችበትን ጋዝ በስሱ እፍ ማድረግ ብቻ ይበቃ ነበር እምቢኝ አሻፈረኝ ካሉ፡፡

እሥራኤሎች ከዚያ ድረስ ከሚመጡ ቤተ ክህነቱን እያመሱት የሚገኙት የአባ ጳውሎስ የወንድም ልጆችም እኮ ይበቁ ነበር ጽላቱን አሳልፎ ለእስራኤሎች ለመሸጥ፡፡ ኮማንዶ ከእስራኤል ድረስ መጥቶ አክሱምን ከሚያሸብር፡፡ለመሆኑ አክሱም በእስራኤል ስትሸበር የወያኔ ወታደር የት ነበር? ዛሬ ከአስራ ስምንት አመት በኋላ ዜናው የተናኘው ለምንድነው?

አለ ነገር!አለ ነገር!እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ ነው ያለው አቀንቃኙ? ምናልባት የጀማል አብዱል ናስር የቀልድ ምጸት ባንድነት ቆመን ለመታገል ይረዳን ይሆን? ቀልዱ እንዲህ ነው፡፡

አንዱ አካሉ ለወሲብ ዝግጁ ባለመሆን ደዌ በመጠቃቱ እኽ! ሊል ወደ አዋቂ ያመራል፡፡ታምራት ገለታ ጋር አይደለም፡፡ግብጽ አገር ነው፡፡ታድያ

ችግሩን ለቃልቻው ካወጋ በኋላ፣ ቃልቻው ለመፍትሄ የሰጠው ክታብ ጭራሽ አላስተኛ ብሎት ፋታ አልሰጠው እያለ 24 ሰዓት ዘብ ቢያቆመው፣ ይህ ቃልቻ ምን አይነት ክታብ ቢሰጠኝ ነው እንዲህ ያደረገኝ ብሎ ክታቡን ተርትሮ ይመለከታል፡፡ ለካስ ቃልቻው የሰጠው የጀማል አብዱል ናስርን ፎቶ ነበር ምነው  ምን በደልኩህ ማለት? ቃልቻውን፡፡ ቃልቻውም መለስ አርጎ ታድያ ምን ከፋህ? ጀማል አብዱልናስር እንኳን ያንተን እቃ መላውን የአረብ ዘር በስድስቱ ቀን ጦርነት ቀጥ አድርጎት አብሮ አቁሞት የለም ወይ ማለት፡፡ እኛስ ተባብረን ለመቆም የማንን ክታብ እንሰር?  ሸገር ሰሞኑን በዚህ ወግ ሞቅ ደመቅ ብላለች አሉ፡፡አዝማሪዎችም የማሲንቋቸውን ለዛ፥ በዚህ ግጥም እያዋዙት እንደሚገኙ ተሰምቷል፡፡

ወይ፡ጥልያን ወይ ጥልያን ቂም አልረሳ ብለኸ፣

ውጫሌን ደገምከው የአባን አፍ ለውጠኸ፣

ቋንቋውን አጣርሰህ የዘላበዱትን፣

ለምን ነው ያተምከው አባ የሸወዱትን ፡፡

በሉ እንግዲህ ራቢን ሙሼ ላቲንን በወጉ ባይችሉም ጳጳሱን ሸውደው አሸንፈዋል፡፡ አባ ጳውሎስ ግን ተሸውደው አይደለም ተስማምተው ነው፡፡

በቸር እንገናኝ

እንግዳ/ ከኖርዌ